# ኢትዮጵያዬ

ከዳዊት ተመስገን

ኢትዮጵያዬ የልምላሜ ምድር

የተከተበልሽ የታሪክ ዝክር

ምነዋ? አምላክ ፊቱን አዞረብሽ

የተቀደሰሽ ቅድስት አገር

የሰው ዘር መገኛ ምንጭ እንዳልተባልሽ

ምነው? ባዶ ሆነ ጎተራሽ

በለምለም ምድርሽ የዘራሽው

በተራራ..... በሸለቆሽ በረግረጉ ያበቀልሽው

ዕፅዋት አዝርዕት ጥቅጥቅ ያለው ጫካሽ

ወንዙ በያለበት ፏፏቴው ጅረትሽ

የአምላክ ዝናብ አልበቃ አለው?

ምነው! ልጆችሽ ረሃብ አገኛቸው?

ህጻን ጎልማሳ አዛውንትሽ

ቄስ ሼኩ ቀሳውስትሽ

ምሁር ቀራጩ አዝማሪሽ

የየዕለቱ ወግ ጨዋታው

ምነው ሰቆቃ ሆነ ዜማው?

"ከዚህ ሌላ ትዝብት ውረሽ

ሳይነጋ እንዳስመሸሽብኝ

ጊዜና ትውልድ ይፍረደኝ

ሳልነቃ እንዳስፈረድሽብኝ"

ብሎ ቴዎድሮስ የረገመሽ

መቅደላ አፋፍ ላይ ቆሞ

ልናየው ይሆን ዛሬ?

ብርሃን በቀን ጨልሞ

እባክሽ... ንገሪኝ እማምዬ

አረንጓዴ ውበትሽ ጠፍቶ

የረሃብ መዲና መባሉ

አምሮሽ ይሆን ዋይ ኢትዮጵያዬ

እባክህ አምላኬ ተለመናት

ልጆቿ በረሃብ አለቁ አታሰኛት

በረሃብ አርጩሜ ጠበስካት

ኧረ በስንቱ ፈጀሃት

ኧረ መቼ ነው በቃ የምትላት

ችግሮቿ በላይ በላይ ሲደራረብባት

እጆቿን ዘርግታ ስትለምንህ

ዳግም በችጋር ቸነፈር አትቅጣት

ኢትዮጵያን! አምላክ እባክህ ተለመናት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የድል ባለቤት ይሆናል!

እናቸንፋለን!!

20 Nov 2015